## ምሥለ ወያኔዎች

ከዓሣዬ

ግንዷን ኢትዮጵያን ፡ እየቦረቦሩ
ከቅርንጫፍ መንጠልጠል ፡ ከሆነ ቀመሩ
ውጤቱ እንደታየው ፡ ሕዝብን ኣራርቆ ፡ ድንበር ማሥደፈሩ
ተጣቦ ሲነሣ ፡ ገና ከጠዋቱ ፡ ገና ከጅምሩ
እሱ ኣልነበረም እንዴ ፡ የሻቢያ ውድቀት ፡ የወያኔ ክሥረቱ ?
እኮ እንንገራችሁ !
የጎጥ ኣመንዝራ ፡ ኣደንቋሪ ጩኸት ፡ ሌላ ሣይሆን ትርፉ
ሕዝብን ኣፈናቃይ ፡ ዕልቂትን ቀፍቃፊ ፡ ነውና ውጤቱ
ኣንድነትን ኣፍራሽ ፡ ኣገርን በታኝ ነው ፡ ሥረ መሰረቱ ።

ኣንቀጽ 39ኝን ፡
ከወያኔ በላይ ለኦሮሞው ይጠቅማል ፡ እያለ ከማለ
በጎጥ ተሸንሽኖ ፡ በዓማራነት ቅዥት ኢትዮጵያን ካገለለ
በጽንፈኛ ዓላማው ፡ ልክ እንደ ወያኔ በቦዩ ከፈሰሰ ፡
ዓማራ ኦሮሞ በሚል ዘረኝነት ፡ ከተጠለፋችሁ
መልሣችሁ ምን ይሆን ፡ እሥቲ እንጠይቃችሁ
ከዘረኛውና ፡ ከትግራዩ ወያኔ ፡ በምን ተሻላችሁ ?

ዘረኛ ኣንጃ ባንዳ ጠባብ የሆናችሁ
በወያኔ ሶልዲ በጥቅም ተገዝታችሁ
ምሥለ ወያኔዎች ፡ ተውን እባካችሁ
ምነው በኣገር ላይ ፡ ምነው በወገን ላይ
ትግሉ እንዳይጎለብት ፡ እሾህ ኣሜኬላ ፡ ጋሬጣ የሆናችሁ ? ።

ምሥለ ወያኔዎች ፡ የሥም ተቃዋሚ ፡ ሎሚ መሥሎ እንቧይ
ትግሉ በኣገር ቤት ፡ ተጠናክሮ ሲታይ
ሕብረት መሥርታችሁ ፡ ጠባብ ጎጠኛውን ፡ ማጥቃት ሲገባችሁ
በተገላቢጦሽ ፡ ትግሉን ለመበተን ፡ ሥራዬ ያላችሁ
ኢሕኣፓን በማውገዝ ለዘረኛው ጠባብ ግዳይ የጣላችሁ
ተነቅቶባችኋል !
ከወያኔ ጋራ ፡ በቃል ኪዳን ቁርባን ፡ ጥምረት መፍጠራችሁ ።

ከእንግዲህስ ወድያ ፡
በተቃዋሚ ጭምብል ፡ ከወያኔ ጉያ ተሸጉጦ ጉራ
እሥቲ እንግዲህ ይብቃን ፡ ግዜው ኣልፏልና
ከጠላት ወግኖ ፡ ኣገር ለመበተን ፡ በሚፈጸም ደባ
ኢትዮጵያ እንደሁ ኣትፈርሥ ፡ ጀግኖች ኣሏትና
በመሥዋዕትነታቸው !
ዘላለም ትኖራለች ፡ ውዲቷ ኣገራችን ፡ ታፍራና ተከብራ !

04/09/2017 GC